# ኢሚግሬሽን በርዎን የሚያንኳኳ ከሆነ እርስዎ መብቶች አሉዎት!

## በሩን አይክፈቱ።

በህጉ መሰረት፣ የኢሚግሬሽን ባለስልጣኖች በወንጀል ፍርድ ቤት ዳኛ የተፈረመበት ማዘዣ ወረቀት ሳይይዙ ቤትዎ መግባት አይችሉም። የኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖችን የማዘዣ ወረቀቱን በበሩ ሥር እንዲያስገቡ ይጠይቋቸው። ኢሚግሬሽን የሚያመጣው የማዘዣ ወረቀት አብዛኛውን ጊዜ የሚፈረመው በኢሚግሬሽን ባለሥልጣን ብቻ እንጂ በዳኛ አይደለም።

## ዝም ብለው ይቆዩ።

ዝም የማለት መብትዎን ለመጠቀም እንደሚፈልጉ ለኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖች ይንገሯቸው።

## አይፈርሙ።

ከጠበቃ ጋር ሳይነጋገሩ የኢሚግሬሽን ባለስልጣኖች የሚሰጡዎትን ማንኛውንም ነገር እንዳይፈርሙ።